# አረብ ወደ እኛ ለግብርና እኛ ወደ አረብ ለግርድና

የዛሬውን አያድርገውና ፈረንጅ ሁሉ ማኮሮኒና ፓስታ እያለ የሚበላውን ስንዴ፣ ኤስፕሬሶ፣ ማኪያቶ እያለ እያማረጠ የሚጠጣውን ቡና፣ ጥሙን የሚቆርጥበትን የቢራ ገብስ ለአለም ያበረከቱት የኢትዮጵያ ገበሬዎች ነበሩ። ዘመኑ ዘመመና የበዪ ተመልካች ሆነው በኩራት ምትክ አንገት መድፋት፣ በመለገስ ምትክ መለመን የእለት ተእለት ኑሮአቸው ሆኖአል። ይህ አሳዛኝና አሳፋሪ ድራማ ከአመት አመት እየተደጋገመ የተከበረችው ሃገራችንን የለማኞች መለያ አደረጋት። የኦክስፎርዱም መዝገበ ቃላት ስለረሀብ ሲገልጽ ኢትዮጵያን በምሳሌነት አሰፈራት። ይሁን እንጂ በኛው የእድሜ ዘመን ጃንሆይ ግሪክን ችጋር በጎበኛት ወቅት በርካታ ሰንጋዎች በመርከብ አስጭነው መላካቸውን፣ የቤልጅየም ሕዝብ በተቸገረ ወቅት ብርድልብስ አስጭነው መላካቸውን እናስታውሳለን። ኢትዮጵያ ለዘመናት ስደተኞችን ስታስተናግድ ኖራለች የግሪክ፣ የአርመን፣ የአረብ ሀገራት እስራኤልንም ጨምሮ ከዚህ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። ይህ ሁሉ ቀረና የዛሬዎቹ መሪዎች የኢትዮጵያን ልጆች በአራቱም ማዕዘናት እንድንበተን ያሳድዱናል።

ይሁን እንጂ የነገውን ሕይወታችንን በተሻለ አቅጣጫና ደረጃ እንመራዋለን ከሚለው ራዕይ ይልቅ ትናንት አገራችን ጥጋብ ነበር እያልን በሰቀቀን የሁዋልዮሽ የምናስብ ከሆነ የዛሬዋም ቀን ለነገ የድሮን ያህል ልትርቅብን መቻሏ እውነት ነው። እንደ ገዢዎቻችን ሁሉ የራዕያችን ጣርያው ‘በቀን ሶስቴ መብላት’ ብቻ ከሆነ ግጦሽ ፍለጋ ወዲያ ወዲህ ከሚል እንስሳ የምንለየው በጥቂቱ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ሰው ለመብላት የሚኖር ሳይሆን ለመኖር የሚበላ ፍጡር ነውና የሚረካው በእውቀት ሲያድግና በስልጣኔ ሲመጥቅ ነው። ስለዚህ ሰብዐዊ ፍጡርን ከርስ መሙላት ብቻውን ምሉዕ አያደርገውም። ሰው በዳቦ ብቻ አይኖርም ይለዋል መፅሀ የሚለው መጽሀፉ! የትግራይ ተገንጣይ ቡድን መሪዎች ይቺኑ ሆድ የመሙላት ራዕያቸውን እንኳ ወደ እውነታ ማምጣት አቅቷቸው እንኳንስ ቀደም ሲል ረሀብ የተደጋገመበት የአገራችን ክፍል ይቅርና ጥጋብ የነበረበትም ይኸው በጠኔ የሞቱትን ልጆቹን መቅበር እጣው ሆኖአል።

ከቅኝ ግዛት በሁዋላ የአፍሪካ ችግር አልቀረፍ ያለው ጥሬ እቃ አቅራቢ ብቻ በመሆንዋና ምርትዋን እራሷ ወደ ኢንዱስትሪ ውጤት ለመለወጥ ባለመትጋትዋ ነው እየተባለ ሲነገረን ብዙ ዘመናት አለፉ። እርግጥ ነው የአፍሪካ ልጆች የብረት ማዕድናችንን ሸጠን ድስት ከውጪ ስንገዛ፣ ፍራፍሬውን በርካሽ ለውጭ ሸጠን ጭማቂ እየተባለ ታሽጎ የሚመጣውን የምግብ ቀለምና ስኳር የተሞጀረበትን ውሀ አሥር እጥፍ ከፍለን ስንጋት፣ ‘ኦርጋኒክ ቡና ሸጠን ‘ኔስካፌ’ ስንጠጣ፣ ጥጡን በርካሽ ሸጠን ህንድና ቻይና የተሰፉ ልብሶችን በውድ ስንገዛ ይኸው ዛሬን ድረስ አለን። ይባስ ተብሎ አገር በቀል ፋብሪካዎች ያመርቱ የነበረውን ልብስና ጫማ በ ‘ሞተከዳ ወይም ሳልቫጅ’ ተክተን ፋብሪካዎቻችንን ዘግተን ቁጭ አልን።

ያለመታደል ሆኖ እናውቅላችኋለን ያሉ ፈረንጆች ባሰመሩልን የድንበር ክልል እየተጋጨን ፈረንጆች በሚሸጡልን መሳርያ ስንጫረስ፣ ፈረንጆች ባለሰላምና ባለጸጋ የአፍሪካ ልጆች ደግሞ የነጻነት ባንዲራ የምናውለበልብ ግን ሰላም ያጣን ድሆች ሆንን። ቁልቁል ወርደንም ስልጣን በጠማቸው አምባገነኖችና ትናንሽ ንጉስ መሆን በከጀሉ ሃሳበ ትንሾች በጎጥና በመንደር ተሸንሽነን እንድንናከስ ያደርጉናል። ተመልሰን ፈረንጆችን የአስጥሉን አቤቱታ ይዘን ሸቅብ ቁልቁል ስንል ለስቃያችን የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ እያድበሰበሱ ‘ተስፋ ቢስ ሀገሮች’ የሚል ቅጽል ስም ይለጥፉብናል። ገዢዎቻችንም በሥራ ከመታወቅ ይልቅ በልመና መሰልጠንን ሙያቸው አድርገው ከለመኑት እየሰረቁ መኖርን ተያይዘውታል። አሁን አንድ ፊቱን ጥሬ እቃ ከመቸብቸብም ዝቅ ተብሎ ከስልሳ እስከ ሰማንያ በመቶ የሆነው ሕዝብ የሚተዳደርበትን መሬት ማለትም ሀገራቸውን በጅምላ መሸጡን ተያይዘውታል።

አፍሪካ በጠቅላላው ስትታይ ይህን ብትመስልም አድዋ ላይ የበቀሉ የሰው አረሞች ግን ከዚህ የከፉ ተልዕኮ ይዘው በፍጥነትና በእርግጠኛነት እየገሰገሱ ነው። የራሱን ሥጋ መልሶ እየበላ የሚጠረቃ እንሥሳ ከወያኔ በቀር አልተፈጠረም። ኢትዮጵያን በጠቅላላው እንተውና ቆመንለታል የሚሉትን ህዝብ አንዴ ዝልዝል ጥብስ ሌላ ጊዜ ግንፍልፍል እያደረጉ ከመብላት ያልተናነስ ክፋትን ፈጽመውባቸዋል። በረሀብ የሚቆላ የትግራይን ሕዝብ እንደ እንስሳ ነድተው ሜዳ ላይ ካሰፈሩ በሁዋላ አሸዋ እንደ ማሽላ ሸጠው በአንድ ጀንበር 40 ሚልዮን ዶላር መቀበልና እፍኝ እንኳ ማሽላ ለተራበው ሕዝብ ያለመስጠት ምን ማለት እንደሆነ ምናልባት እራሱ የትግራይ ሕዝብ ያውቀው ይሆናል። እኒህ የአእምሮ በሽተኞች ዛሬ የትግራይን ሕዝብ ከወገኑ ከቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በማጋጨት ለራሱ ለትግራይ ሕዝብ የሚያቆዩለት መከራ ተዝቆ የሚያልቅ አይሆንም። ኢትዮጵያን በሀራጅ በመሸጥ ትግራይን እገነባለሁ ብለው ደፋ ቀና ሲሉ እውነት የመሰላቸው ተላሎች ለልጅ ልጆቻቸው የሚተርፍ ጥላቻን ብቻ ታቅፈው ይቀመጣሉ። እንደተለመደው የአምባገነኖች ባህሪይ ሁሉ የወያኔ

መሪዎችም ቀን ዘንበል ሲልባቸው ሕዝቡን ለመከራ ዳርገው የዘረፉትን ገንዘብ ሰብስበው እንደሚጠፉ ያለመገመት አጉል መበለጥ ነው።

ወደ ጀመርኩት አርእስት ልመለስና በግብርና ሞያ የሰለጠኑ የኢትዮጵያ ልጆችና በሙያው ሊሰማሩ የፈለጉ ባለሀብቶች ይህንን የሥራ ዘርፍ እንዲያሳድጉት ከማበረታት ይልቅ ተስፋ እያስቆረጡአቸው ከብዙ መንገላታት በሁዋላ እውቀታቸውንና ገንዘባቸውን ይዘው ወደሌላ አገር እንዲሄዱ ይገደዳሉ። በተቃራኒው አፍራሽ የሆነ ዘረኛ ፖሊሲ የሙጥኝ በማለት ለአለም ሕዝብ የተረፉ ገበሬዎች በቀን አንዴ መብላትም እንዳይችሉ ተደርገዋል። ከኢትዮጵያዊው ይልቅ ሕንዶቹ፣ ኮርያኖቹ፣ ቻይናዎቹና አረቦቹ የሀገራችንን መሬት ተረክበው የፈለጉትን ለማድረግ ሁኔታው ሁሉ ይመቻችላቸዋል። ለነኚህ የውጭ ሰዎች የሀገራችንን መሬት ለመቀራመት የሚመቻችላቸው ከኢትዮጵያዊው የተሻሉ ሆነው ሳይሆን በሕዝባችን ላይ ይበልጥ ግፍና በደል ለመፈጸምና ያለ ችግር ገንዘብ ለመዝረፍ የሚያመች ስለሆነ ብቻ የተደረገ ሀገር የማፍረስ ተልዕኮ ነው።

ብናኝ አፈር እንዳይሄድ ጫማ ያሳጠቡ ትውልዶች አልፈው አገር ለባዕድ የሚሸጡ የትውልድ ዝቃጮች ተተኩ። እናም ባለ አገሩ ከቀዬው እየተፈናቀለና በሰፊው ሊያመርት የሚችልበት መሬትም እየተነፈገው አረቦችና ሕንዶች የራሳቸውን ሕዝብ የሚመግቡበት መሬት በገፍ ይሰጣቸዋል። የኢትዮጵያ ገበሬዎች ግን ከአመት አመት ምጽዋት ጠባቂ ረሀብተኛ እንዲሆኑ ተፈርዶባቸዋል። ሕዝቡን በቀን ሶስቴ እንዲበላ የማድረግ የወያኔዎች ራዕይ ግን ከቶውንም የሚሳካላቸው አይሆንም። የዚህ አጥፊ የወያኔ ባህርይ ውጤት የኢትዮጵያ ልጆች ትራፊ ፍለጋ ተሸፋፍነውና ስም ለውጠው "**…. አረቦች ወደ ኢትዮጵያ ለግብርና እኛ ወደ አረብ አገር ለግርድና….**" እያሉ እያለቀሱ ክብራቸውን ዝቅ አድርገው ወደ አረብ አገር እየተሰደዱ ነው።

በመጨረሻም ለአዲስ ዐመት መልካም ምኞቴን ላሰፍርላችሁ ስል የሚሌንየም በዐልና የአቶ ገብረ መድኅን አርአያ ቃለመጠይቅ ውልብ አሉኝ። አቶ መለስ ወደ እናታቸው ወደ ኤርትራ እንደሚያዘነብሉ ሁሉ ወ/ሮ አዜብም ወደ አባታቸው ወደ ሱዳን ሊያደሉ እንደሚችሉም ገመትኩ። የሚሌንየም ድግስ ላይ የተዘፈነውን የሱዳን ዘፈን፣ የክብር እንግዳውንና የጌቶቹን ዳንስ በሃሳብ ቃኘት አድርጌ ለካስ ለሱዳን የተሰጠው መሬት እንደ ጥሎሽም ኖሯል ብዬ ከት ብዬ ሳቅሁኝ።

መጪው ዘመን የፍቅር፣ የሕብረትና የአንድነት ይሁንልን። ልጆቻችንን ከግርድና አረቦቹንም ከግብርና አስወጥተን ሰብዓዊ ክብራችንን የምናስጠብቅና ሀገራዊ ግዴታችንን የምንወጣ ጠንካራ ዜጎች እንሆን ዘንድ እመኛለሁ። የተበተኑ ወገኖቻችንና የእናታችን የድንቅነሽ አፅምም ወደሀገራችን የሚመለሱበት ዘመን ቅርብ እንዲሆንልን እግዚአብሄር ይርዳን።

ዳኛቸው ቢያድግልኝ

biyadegelgne@hotmail.com